# ታላቅ የተቃውሞ ጥሪ

## በቶሮንቶና አካባቢው ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ

ኢትዮጵያ አገራችንን በጎሣና በሃይማኖት ከፋፍሎ ላለፉት 20 ዓመታት ያህል በነፍጡ ብርታት እየገዛ ያለው አረመኔያዊው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፣ በሰሜን አፍሪቃና በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች እየተቀጣጠለና አምባገነኖችን እንድ ባንድ እየናደ ያለው የለውጥ ቋያ ወደ ኢትዮጵያም ማቅናቱ የማይቀር መሆኑን ስለተገነዘበ ከዚህ የሚያመልጥበትን መንገድ በመሻት የሚችለውን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህ በእንዲህ እያለም፣ የአገራችንን አንዳንድ እውነታዎች ስንዳስስ፦

- በሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ልጆች በጎጠኛው ሕወሓት/ኢሕአዴግ ማጎሪያዎች ተወርውረው በመሠቃየት ላይ ይገኛሉ። ከድብደባና ግድያ የተረፉት ደግሞ ሕይወታቸውን ለማዳን በብዛት አገር ለቅቀው እየተሰደዱ ነው፤
- በርሃብ እየተሠቃየና የሚላስ-የሚቀመስም አጥቶ እጅግ አሳዛኝ በሆነ መልኩ ሕይወቱን ለማቆየት ከውሻና ከድመት ጋር እየተጋፋ በቆሻሻ ገንዳ ውስጥ የተጣለ የምግብ ትራፊ የሚሻማው የወገናችን ቁጥር እየጨመረ መምጣቱንና
- በገጠሪቱ ኢትዮጵያም ሰፋፊ ለም መሬቶች ከድሀው አርሶ አደር እየተነጠቁና ለባዕዳን እየተቸበቸቡ መሆኑን እንሰማለን።

እነዚህንና እነዚህን የመሣሰሉ ግፎችን በወገናችን እየፈጸመ ያለው ገዢ ቡድን ይህ ሁሉ ግፍ አልበቃ ብሎት ዛሬ ደግሞ በስደት ላይ የሚገኘውን ወገን በጥቅማ-ጥቅም በመደለልና "ኢንቬስት አድርጉም" በማለት ሊያደነቁረን የጥፋት መልዕክተኞቹን ወደሰሜን አሜሪካ በማሠማራት ላይ ይገኛል። በቶሮንቶም ተመሳሳዩን ስብሰባ April 10, 2011 ለማድረግ ዕቅድ እንዳወጣ መረዳት ችለናል። ስለዚህም የዚህን ጎጠኛ ሥርዓት መልዕክተኞች በሥፍራው ተገኝተን የተቃውሞ ድምፃችንንና የሕዝባችንን ብሶት ለማሠማት ሠላማዊ ሠልፍ የጠራን ስለሆነ በዕለቱ እንድትገኙልን ወገናዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

**የተቃውሞ ሠልፍ አስተባባሪ ኮሚቴ***

**ቦታ** 89 CHESTNUT St. **ቀን** April 10, 2011 **ስዓት** **12:30** pm -
**Chestnut Residence Conference Center University of Toronto**